# በወገን ቁስል ላይ ጨው መነስነሱ ያብቃ

ኢትዮጵያውያን ያልታደልን፤ መከራ በመከራ ተቀባይ ሆንና በቁስላችን ጨው ነሽናሾች በርክተውብን አሉ። ዛሬ በሳውዲ አረብያና ሌሎች አረብ ሀገሮች በዜጎች ላይ ግድያና ግፍ እየተፈጸመ ባለበት ኢትዮጵያውያን በሚገባና በሚጠበቅ ንዴት እሪ ሲሉና ሲሰለፉ ጠባብ የፖለቲካና አልፎም በዘቀጠ ደረጃ ዝርፊያ ዓላማቸው የሆኑ ደግሞ በዜጎች ስቃይ ላይ ሊነግዱና ፖለቲካ ትርፍ ሊያገኙ እየተራወጡ ናቸው። በጣም የሚያሳዝንና ሊወገዝም የሚገባው አሳፋሪ ጥረት ነው። ይበልጥ የሚያሳዝነው ደግሞ የመጀመሪያው አለመሆኑ ነው።

ክስተቱ አዲስ አይደለም። ከዚህ ቀደም እህቶቻችን በሊባኖስ ተበደሉ፤ ተገደሉና ተሰቃዩ በሚል በዚያ ያሉትን ለመርዳት ብለው ገንዘብ ሰብስበው ድራሻቸው የጠፋ ጥቂት አልነበሩም። በውጭ ሀገር ያለው ኢትዮጵያዊ የቀን ሐሩር እየጠበሰው የሌሊት ቁር እያሰቃየው ለፍቶ ግሮ ጥሮ ተሰቃይቶ ያገኘውን ገንዘብ በሰበብ አስባቡ የዘረፉት ጥቂቶች አልነበሩም። አንድ ስብስብ ለምሳሌ ከሚሊዮን ዶላር በላይ ተዋጥቶለት ሁለት ሶስተኛው የት እንደገባ ሳይታወቅ ቀርቷል። ተመልሶ ግን አዋጡ ሲላቸው ዜጎች ገንዘባቸውን ሰጥተዋል። አላፊ አግዳሚው በውጭ ነዋሪ ወገኖችን አልቧል፤ ቀልዶባቸዋል። ከብሮባቸዋል። ሀቅ ያንቃል ቢሉም ሀቁ ግን ይህ ነው። በአሁኑ ጊዜ ወገኖቻችን በሳውዲ አረቢያ ሲገደሉ፡ ስየል ሲቀበሉ፤ ሲዋረዱና ኢሰብዓዊ እርምጃ ሲወሰድባቸው ቀሪው ኢትዮጵያዊ በሚገባ ተናዶና ተነክቶ የተቃውሞ ሰልፍ ተባብሮ ሲያደርግ ይህን ደግፎ በመነሳት ፊንታ የፖለቲካ ንግድ ሊያቀላጠፉ የተነሱት ማፈሪያ ክፍሎች የሚወገዙ ናቸው። የወገን መከራና ሰቆቃ ጉዳያቸው አይደለም። ያለውን የተቃውሞ ጥረት አኮላሽተው የራሳቸውን ፖለቲካዊ የበላይነት ማስፈንን ይፈልጋሉ። እየሰራ ያለውን አስተባባሪ ግብረ ሀይል ኣፍርሰው ሌላ ማቋቋም ይጥራሉ። ለምን ቢባሉም መልስ የላቸውም። ጥረታቸው ደግሞ ያሉትን አግላይ ነው -- ኢፖእአኮን ያስወግዳል፤ ሙስሊም ዜጎችን ያርቃል፡ ለተወሰነ ድርጅት ወይ ድርጅቶች የሚያድር ነው። በአጭሩ ከለልተኛምና ዘረኛም ነው። ይህ ነው ታዲያ አስተብባሪ ሆኖ አደራጅ ሆኖ መፍትሔ ሊያመጣልን የሚችለው? መልሱ አይደለም ነው። ሆኖም ባለፉት ተሞክሮአችን እንዳየነው የማደናገሪያ ችሎታቸው ቀላል አይደለም። ሀገር ውዳዱ ዜጋ ደግሞ ማመዛዘንን በቁጭትና ንዴት የተነካ ስለሚመስል ትላንትን እየረሳ ነጋ ጠባ ይበዘበዛል መጫወቻቸውም ይሆናል። ይህ መቆም ያለበት ነው።

ይባስ ተብሎ አሁንማ ዋና አደራጅና አሰባሳቢ ተብለው የተሰየሙብን የቀይ ሽብር ወንጀለኞች (ኣቅዋም ለውጠናል ቢሉም ዛሬም ለወያኔ የሚሰሩ)፤ ለባዕድ ያደሩ፤ ገንዘብ አሳዳጆች ወዘተ ናቸው። በነዚህ ዳግም መደናገርን ትተን ነቃ ብለን እየሰሩና እየታገሉ ያሉትን ለመደገፍና ለማጠናከር መዋደቅ አለብን።

ለምሳሌ የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ ከተቋቋመ 18 ዓመት የሞላው ሲሆን በዚህ ሁሉ ጊዜ የደገፉት ቢኖሩም ሊያፈርሱት የሚጥሩም በርካታ ናቸው። ምክንያቱ የራሳቸው ነው -- ግን መገመት የሚያቅተን አይደለም። ኢፖእአኮ የተመሰረተው የታሰሩና ደብዛቸው የጠፉ ዜጎች ጉዳያቸውና ስቃያቸው በነበሩት ዓለም አቀፍና የሀገር ቤትም ተቋሞች ከቁጥር ያልገባ በመሆኑ ይህንኑ ጉድለት ለማሟላትና ለድምጽ አልባዎቹ ድምጽ ለመሆን ነበር። የወቅቱ የኢሰመጉ ሊቀ መንበር ፖለቲካን በማስቀደም በተለይም ደብዛቸው የጠፋውን ኢሕአፓዎች ጉዳይ ኣላነሳም ብለው ነበር- በዚህም ብልሹ አቅዋም ገፍተውበት ተከታዮቻቸውም ቀጥለውበታል። አምኔስቲና የሰብዓዊ መብት ጠባቂ (ህዩማን ራይትስ ዋች) የተባሉት ተቋሞች ደግሞ ከየሀገራቸው የስለላ መዋቅር ጋር እጅና ጓንት ሆነው የሚሰሩ ናቸውና ለኢትዮጵያ ድርቅ ብሎ የቆመውን ኢሕአፓን በተመለከተ መዘገብን የተከለከሉ ይመስላሉ። ይህን ሁሉ የዝምታ ጥቃት ለመቋቋም የተቋቋመው ኢፖእአኮ ከዚህ አልፎ የወያኔን መብት ረገጣ ሙሉ በሙሉና የአካባቢውንም ግፍ ሲያጋልጥ ቆይቷል እንጂ የፖለቲካ ልዩነትን አስገብቶ ከለልተኛ ኣልሆነም። ለሁሉ የፖለቲካ እስረኛ ጠበቃና ተከላካይ ሆኖም ቆይቷል፤ ዛሬም ነው። ቢሆንም ከተቋቋመ ጊዜ ጀምሮ ሊያፈርሱት የጣሩ ብዙ ናቸው። አብረውት እንደመስራት ድራሹን ሊያጠፉ የተነሱ ነበሩ/ አሉም። ያፈረሱና የጎዱ መስሏቸውም ሁለት ራሳቸውን ኢፖእአኮ ካናዳ ያሉትንም ማፈሪያ ግለሰቦች እስከማቀፍና የሄዱም ኣሉ። የሰራንና የሚሰራን ድርጅት ማበረታት ሲገባ ለማፍረስ መጣር ሀገርን የጎዳና እየጎዳ ያለም ነው። ይህ ግን ቀጣይ ጠባይ ሆነና በራስ ስራ ድጋፍን ማግኘት ሳይሆን በቅድሚያ ያለውን ማፍረስ ላይ የሚሰማሩ ብዙዎች ናቸው። ሆኖም ግን ሁላችን እንደምንገነዘበው ስም እየቀያየሩ የመጡ ሁሉ ከስመዋል። ገንዘብ አዋጡ እንጂ ትግሉ እኮ አልቋል፤ ድል ነገ ነው ያሉንም ለሀገራችንና ለዴሞክራሲ ሊያበቁን አለመቻል ሳይሆን ከገንዘብ ዝርፊያ ውጪ ሲጥሩም አልታዩም። ነጋ ጠባ አምጣ አዋጣ የሚባለው ዜጋ ያለፈው የት ደረስ ምንስ ሰራችሁበት ብሎ መጠየቅ ግዴታው ነው። በሀገር ወዳድነታችን ላይ የሚቀልዱትን ማጀብና ሰለባ መሆን የለበትም። ደግመን ደጋግመን እንዳልነው ትግላችን የግል ሳይሆን የውድ ሀገራችንን ህልውና የሚመለከት

ነውና እንደ ቧልት መወሰድ የለበትም። ስለዚህም ማንም የሚያሞኘው ሆነን መጫወቻ ከሆንን ሀገራችንን መጥቀም ሳይሆን እየጎዳን ነው። ከዚህ አንጻርም መሪ ወይም መሪዎች ብለን የምናዳንቃቸውና የምናጨበጭብላቸው በርግጥም መሪና ሀገር ወዳድ መሆናችውን ማወቅ አለብን። ስንቱ አድርባይ ነው መሪ ነኝ ብሎ ገንዘብም ዘርፎ ለወያኔ ያደረ? በ ቅንጅትም በህብረትም አይተናል። መርሳት ያስጠቃናል። ስንቱ የደርግ ሎሌና የቀይ ሽብር አጃቢና ወንጀለኛ ነው አቅዋም ቀይሯል፤ ንስሀ ግባ አትበሉት ተብሎ በህዝብ ጎራ ይገባ ዘንድ በር ተከፍቶለት ትግላችንን ያጠቃው፤ እያጠቃም ያለው? ስንቴ የድል ቃል ኪዳን ገብተውልን ጎሕ ሳይቀድ ፈረጠጡ? ወደ ወያኔ ጎራ ገቡ? ለህዝብ የታጋሉትንና ጉዳትም የደረሰባቸውን ረስቶ ድንገት ብቅ ያሉትን ወኔ ቢሶች መሪ ብሎ አቅፎ የተሞኘ ማን ነው?

በቂ ተምክሮ አለን። አግላይ ዘመቻዎች፤ በትግል ሽፋን ሕዝብን መዝረፍ አላቆም ያሉ ጥረቶች ሁሉ የሚደገፉ ሳይሆን የሚወግዙ ናቸው። በራሳቸውም እንደሚከስሙ ከዚህ በፊት ያየነው ነው። እሪ ብለው በዜናች እንባ ላይ ቀዝፈው የጫጫ ቡድናቸውን ሊያገዝፉ የሚጥሩና በዚሁ ሂደትም የሚታገሉትን ሊያጠቁ የሚወራጩት ሁሉ ወዳቂ ናቸው -- ተባብረን አይሆንም በቃችሁ ካልናቸው ማለት ነው። ታሪክ የምንጠቅሰውም ቂም በቀልን ለማራገብ ሳይሆን ዛሬም ቢሆን ወንጀለኞቹና ሽብርተኞቹ፤ ዘራፊዎቹና የህዝብ ትግልን አኮላሾቹ ቅንጣትም ስላልተቀየሩ ነው። አሁንም በሃቅ የሚታገሉትን ለማፍረስ ለማጥፋት እየተረባረቡ ስለሆነ ነው። በሕዝብ ቁስል ላይ ጨው መነስነስ አናቆምም ስላሉም ነው። ትግላችን ኢትዮጵያን ከጥፋት ለማዳን ነውናም ተጫወቱብን ብለን ልንፈቅድላቸው አንችልም።

በደማችንና ሰቆቃችን ማንም ሆነ ማን ሊነግድ መፍቀድ የለብንም !!

ወያኔንም ቅጥረኞቹንም አምርረን እንታገል!!